

አበበ ተክለሃይማኖት (ሜጄር ጄኔራል)

# “ሁለተኛው የጫጉላ ሽርሽር”

## (HONEYMOON)

የመጀመሪያውን ጥፋት እንዳይደግመው የሉዑላዊ ባህር በር መብታችን ጉዳይ ይጠበቅ
Wednesday, 18 July 2018 15:26

አበበ ተክለሃይማኖት (ሜጀር ጄኔራል)

የመጀመርያው “የጫጉላ ሽርሽር” (honeymoon) ከ 1983-1990 የነበረውና ወደ ጦርነት ያመራው ነው። ኤርትራዊያን ነፃነታቸውን በትግል አረጋግጠዋል። እውቅና መስጠት የመርህ እና የቁርጠኝነት ውሳኔ ነበር። ኤርትራ በሌሎች ሀገሮች እና የተባበሩት መንግስታት እውቅና እንድታገኝ ኢትዮጵያ ቀድማ እውቅናም በመስጠት ሚናዋ የላቀ ነበር። “የጫጉላው ሽርሽር” እዚህ ይጀመራል (ቀደም ሲል በሻዕቢያ እና በኢህዴግ በተለይም ከህወሓት ጋር አንዴ ሞቅ ሌላ ግዜ ወደ ግጭት የሚያመራ የሚመስል ግንኙነት ነበር)።

በቀዳሚዎቹ የነጻነት አመታት ኢትዮጵያና ኤርትራ የነበራቸው ግንኙነት ለሌሎቹም በምሳሌነት እንደሚሆን ሲደነቅ የነበረ ነው። ምንም እንኳን በርካታ ኢትዮጵያዊያን ግንኙነቱ ለኤርትራ ጥቅም ያደላ ነው የሚል ቅሬታ ቢኖራቸውም። ከ 1988 ዓ.ም እስከ መጀመሪያዎቹ 1989 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ኢትዮጵያ በአገራቱ መካከል የነበረውን ልቅ እና ቁጥጥር አልባ ግንኙነት ማጥበቅ ስትጀምር የነበረው ግንኙነት ብዙ ሊዘልቅ አልቻለም። በኤርትራ በኩል የነበረው የኢትዮጲያን ሃብት የመዝረፍ ፍለጎት እና ሲመካበት የነበረው ወታደራዊ አይበገሬነት (military invincibility) በመመስረት በግንቦት 1998 ኢትዮጵያ ወረረች።

ኤርትራ ኢትዮጵያን የወረረው በድንበር ጉዳይ አልነበረም:: የሁለቱ አገር የድንበር ኮሚሽነሮች የድንበር መካለሉ እንዴት ይሁን? ብለው በውይይት አዲስ አበባ ተቀምጠም እያሉ ነበር፤ የኤርትራ ታንኮች ሉዓላዊ መሬታችንን የወረሩት። እንደተለመደው የተዛባ ግመግማ (mis-calculation) የኢትዮጵያ መንግስትን ፍትሃዊ የሆነውን ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዝምድና እንዲፈጠር የማስተካከያ እርምጃ እንዳይወስድ ለማስፈራራት እና ብሎም ለማምበርከክ ነበር። ለኤርትራ ሕዝቦች ጭምር ያልረባው ሻዕቢያ ለቡድናዊ ጥቅሙ ሲል በድንበር ስም ኢትዮጵያን ወሮ የሁለቱን ህዝቦች አንድነት አደፈረሰው። ኢትዮጵያም ኤርትራ ወታደሮቿን እንድታስወጣ በመጠየቅ ነገሮች ወደነበሩበት እንዲመለሱ ጠየቀች። “ከባድመ መውጣት ማለት ፀሀይ ጠልቃ ትቀራለች ማለት ነው” በሚል ትዕቢት አሻፈረኝ አለ። ከዚያም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የናዚ ኃይል ግብጽን ለቆ ከወጣ በኋላ በአፍሪካ ምድር በተደረገ ከፍተኛ የሁለት አመት ጦርነት በ 2000 ዓ.ም ኢትዮጵያ የኤርትራን ሰራዊት በከፍተኛ ደረጃ በመደምሰስ ሁሉንም የተያዙ አካባቢዎች ነጻ አወጣች።ኋላም ኤርትራ በአልጀርስ ስምምነት መሰረት በራሷ ይዞታ ነጻ ቀጠና እንዲቋቋም እና የተኩስ አቁም ስምምነትን ሳይወድ በግድ ለመቀበል ተገደደች። ፊቱን ነበረ እንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ እየተባለ ወደ ባሰ የከበባ ስነልቦና (siege mentality) ውስጥ ተዘፈቀ።

በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ማን ያሸንፍ ማንም ሁለቱም ህዝቦች ተጠቃሚ አልነበሩም። ሊሆኑም አይችሉም። በኢትዮጵያ ተፈጥሮ ነበረው ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መነቃቃት ለጊዜውም ቢሆን ተቀዛቅዞ ነበር። በአስር ሺዎች የሚጠጋ የኢትዮጵውያን ወጣቶች ህይወት መቀጠፍ፣ የተፈናቀለው ህዝብ፣ የጠፋው ንብረትና ግዙፍ ነው። መመለስ የማይቻል ነው። ለአገር ሉዓላዊነት ሲባል የጠፋ

ቢሆንም።

ከኤርትራ መንግስት ባህሪ ተነስቶ የኢትዮጵያ መንግስት መዘጋጀት ነበረበት። "የጫጉላ ሽርሽር" ሊያሞኘው አይገበም ነበር። ምናልባትም በዓለም ላይ ምንም ዓይነት ህገ መንግስታዊ ስርዓት የሌላት ብቸኛ አገር፤ በጣም ጨቋኝ ስርዓት የኤርትራ ህዝቦችን እያተራመሰ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቃወሱ እና እየተደቆሱ ብቸኛ አማራጭ ይመስል ወደ ስደት እያመሩ ሀገሪቷ ከመንገዳገድ አልፋ ለመሆኑ እንደ ሀገር ትቀጥላለች ወይስ አትቀጥልም ወደሚል ደረጃ የሚያደርስ መንግስት ተማምኖ እንዝህላልነት ማሳየት አይገበም ነበር።

ግጭት የማስወገድ ተፈጥሯዊ ባህሪውን ያጣ ስምምነት መረጋጋት እና መቋጫ ሊያመጣ አይችልም። መረጋጋት ሊመጣ የሚችለው ሊፈፀም የሚችልበት ሁኔታ ሲኖር ነው። ተፈፃሚነቱ ደግሞ የቀረበውን ስምምነት ለመፈፀም አቅሙና ተነሳሽነቱ ያላቸው ተዋናዮች መኖርን በቅድሚያ ይፈልጋል። አሁን ያለው የኤርትራ መንግስት በሌሎች ሀብት ለመኖር የሚፈልግ መዥገር ነው:: በሌላ መልኩ ኢትዮጵያ ልማት እንዳትጐናፀፍ ከሚፈለጉ ሀይሎች ጎን በመሰለፍ ተመፅዋቾች ሆኖ የተላለኪ ሰራ የሚሰራም ነው። በገለፍ ቀወስ (Gulf Crisis) አሰላለፉ እንዴት እንደተገለበጠ የቅርብ ግዜ ትዝታ ነው። ሰላም የማይፈልግ በሁከት ንግድ የተሰማራ ተላላኪ መንግስት ራሱ በድርጊቱ የሻረዉን የአልጀርስ ስምምነት ተግባራዊ በማድረግ ሰላም ይመጣል ብሎ ማስብ ቂልነት ነው። የባህር በር መብት አስረክቦ ባድመና ኤሮፕ ሰጥቶ ሰላም እናገኛለን ማለት ሞኝነት ነው። በቂ ጥናት እና ዝግጅት የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው።

"የኢትዮጵያ ብሄራዊ ራስ ምታት" ተብሎ የሚጠራው የባህር በር አልባነት ኣባዜ (syndrome) በየግዜው በውስጥ ፖለቲካዊ ትኩሳት ኣንዴ ሲደፈጠጥ ሌላ ግዜ መቃዎሚያ ሲሆን ኖረዋል። አሁን የአልጀርስ ስምምነት ተግበራዊ ከሆነ መብታችንን እስከወዲኛው የማጣት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። የውስጥ ፖለቲካዊ ስልጣን ከዘለቂ የኢትዮጲያ ጥቅም የሚፃረር በሚያስመስል መልኩ ሁሉም መንግስታት በአንዴ ወይም በሌላ መልኩ መበታችንን የራሳቸው ስልጣን ለማደለደል ሲገፈትሩት ኖረዋል። ኤርትራ ነፃ አገር ስትሆን የባህር በር በማጣታችን ኢትዮጵያ አንገቷ ተቆርጧል ብለው ሲጮሁ የነበሩት አንዳንድ ሙሁራን በወቅቱ ባለው ፖለቲካዊ ትኩሳት ታውረው እርግፍ አድርገው ትተውታል። ትግራይን እስከ አዳከመ ድረስ (በአልጀርስ ስምምነት ወደ ኤርትራ የተካለሉት በኢትዮጵያ መሬቶች በአብዛኛው ትግራይ ነው የሚገኙት) የባህር በር ጉዳይ ትተውታል። በትግራይ መድከም የኢትዮጵያ መድከም እንደሆነ በሚያሳፍር ሁኔታ የዘነጉት ይመስላል። "መደመር" ይሉሃል ይሄ ነው። የባህር በር በማጣት ጉዳይ በኢትዮጵያ የህልውና ጉዳይ እንዳልሆነ ጉዳይ እርግፍ አድርገው ትተውታል። በፖለቲከኞች እና ሙሁራን ግዚያዊ ፖለቲካዊ ትኩሳት የምትነዳ አገር ዘለቂ መብትንና ጥቅማ ልታጣ ትችላለች። ከታሪክ ተጠያቂነት እጃችን እናውጣ።

አገራችን የጀመረችው አቃፊ ፖለቲካ፤ ፍቅር፤ ይቅርታና መደመር መሰረት ያደረገ የህዳሴ ጉዞ ይደግ ተመንደግ መባል ያለበት ነው። ከተወሰነ አመታት በኋላ የአገራችን ህልውና አደጋ ውስጥ ሊከተን የሚችለውን የባህር በር እጦት በቸለልተኝነት ዘላቂ ማድረግ የህዳሴ ጉዞውን ማደናቀፍ ነው። ከኤርትራ መንግስት ጋር ያለው "ሁለተኛው የጫጉላ ሽርሽር" (honeymoon) ሳያዘናጋን ኳታር (Qatar) የባህር በር ባይኖረት ምን ትሆን ነበር? ብለን ዴሞክራሲ እንደ ጠላት የሚፈርጀው፤ ቀይ ባህርን ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠር ፍለጎት ያለው፤ የኢትዮጵያ ትልቅነት እንደ ስጋት የሚመለከት፡ ፔትሮ ዶላር (petro dollar) ያሰከረውና በወታደራዊ አቅሙ ተማምኖ የመንን የወረረ የቅንጅት ሓይል ባለበት የመካከለኛ ምስረቅ ተዝረክረከን መቆየት ይቅርታ የማይሰጠው ነው።

## የኢትዮጵያ ሉዓላዊ የባህር በር መብት

በዚህ ፅሑፍ ከዓለም ህግ ኣካያ ኢትዮጵያ ሉዓላዊ የባህር በር መብት እንዳላት እና የአልጀርስ ስምምነት የሃገራችን መብት እና ጥቅም የሚያሳጣ መሆንና ስምምነቱን ለመሻር ሕጋዊ መበት እንዳለን የሁለተኛ ድግሪ መመረቅያ ቴሲስ (1999) መሰረት በማድረግ አቀርባለሁ። የተያይዝነውን የለውጥ ሂደት ለማስፋትና ጥልቀት እንዲኖረው ለማድረግ ሉዓላዊ የባህር በር መብት ወሳኝ መሆኑን በማመን።

ኢትዮጲያ እና ፈረንሳይ እንደ ኢ.አ በ 1897 ባደረጉት ስምምንነት በጂቡቲ በኩል ሊኖረን የሚችለውን የባህር በር ጥያቄ በይፋ (officially) ኣሳልፈን ሰትጠናል። በተለያዩ የውጭ ሓይሎች ተፅእኖ ምክንያት በኤርትራ በኩል ባሉት ወደቦች እንደፈለግነው ባንጠቀምባቸውም ኢትዮጲያ ሉዓላዊ የባሕር በር መበት የይገበኛል ድመቆ የሚነገርለት ነበር። በቅኝ ኃይሏ ጣሊያን እና ኢትዮጵያ መካከል እንደ አ.አ አቆጣጠር 1900፣ በ 1902 እና በ 1908 የተደርጉ ስምምነቶች ግን አትዮጲያ ለመጀመሪያ ግዜ ያውም ጦርነት አሸንፋ ሉዓላዊ የባሕር በር መብት ኣሳልፋ ሰጥታለች።

ኤርትራ በፌደሬሽን ወደ ኢትዮጲያ ከተቀላቀለች በኋላ እንደገና ሉዓለዊ የባሕር በር መበት ማረጋገጥ ችለን ነበር። ከአርባ ኣመታት ባለመብትነት በኋላ ኤርትራ ነፃነትዋ ስትጎናፀፍ አገራችን እንደገና ያለ አግባብ ወደብ የለሽ ተባለች። በጦርነት አሸንፈን መብታችንን አሳለፍን መስጠት ባህላችን እስኪመስል ድረስ የኤርትር ወረራ ከቀለበስን በኋላ የሃገራችን መብት እና ጥቅም የሚያሳጣውን የአልጀርስ ስምምነት ተዋዋልን። አገራችን እስከ ወዲያኛው የባህር በር በምታጣበት ጫፍ ላይ ትገኛለች። በኢትዮጵያ ህልውና ውስጥ የባህር በር የማግኘት ጉዳይ መፍትሔ የሚሻ ወሳኝ ነገር ነው። ጉዳዩም በስልጣን ላይ ካለው መንግስት ባሻገር ሊታይ ይገባዋል። የኤርትራ ህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትና ነፃነትም እውቅና እሰጣለሁ። ነገር ግን የኤርትራ ነፃነት እና የኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት ሉዓላዊ መብት አንዱ ሌላውን የሚተካ (exclusive) እንዳልሆነ አምናለሁ።

## የ 1900፣ 1902 እና 1908 ስምምነቶችች ጣልያን የጣሳቸው ኢትዮጵያ በሕግ የሻረቻቸው ናቸው

የአልጀርስ ስምምነት የተሻረውን በ 1900 ፣በ 1902 እና በ 1908 የተደርጉ ስምምነቶች መሰረት ያደረገ ነው።

በነዚህ ስምምነቶች መሰረት በኢትዮጵያ በኩል ይቀርብ የነበረው ተደጋጋሚ የድንበር መዋሰን ጥሪ በጣሊያን በኩል ሰሚ አላገኘም። ይልቁንም በተለያዩ አካባቢዎች ጦሯን ታደራጅ ነበር። ጣሊያን ስምምነቶችን በቀና መንፈስ ለመፈፀም ዝግጁ አልነበረችም። በዚህም በ 1928 ዓም ኢትዮጵያን ስትወር የነበራት ድብቅ ዓላማ ተጋለጠ። ኢትዮጵያን መውረር ብቻ ሳይሆን የጣሊያን ምስራቅ አፍሪካን ቅኝ ግዛትን ለመመስረት በነበራት እቅድ የሶማሊያ፣ ኤርትራ፣ እና ኢትዮጵያን ድንበሮች ደባልቃ አምስት ግዛቶች ያሉት የጣሊያን የምስራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት ተመስርተ። በዚህ አረመኒያዊ ውሳኔ ጣሊያን ኢትዮጵያን እንደ ሀገር የማጥፋት እና ስሟንም ከታሪክ ማህደር እንዲቀረፍ ፈልጋ ነበር። በአምስቱ ዓመታት የጣልያን ወረራ ዘመን እነዛ የ 1900 ውሎች የሚያስፈፅም አንዱ ወገን (ኢትዮጵያ) ህልውና እንዳይኖረው ተደርገዋል። የቬይና ድንጋጌ የስምምነቶች ህግ በአንቀጽ 60 በሁለትዮሽ ስምምነት ውስጥ በአንዱ አካል የሚፈፀም የህግ ማፍረስን የተመለከቱ ጉዳዮች በሌላኛው አካል ስምምነቱን ለማቋረጥ ወይም ተፈፃሚነቱን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለማቆም መብት ይሰጣል ይላል። በሌላ አነጋገር አንዱ ወገን ስምምነት በመጣሱ ምክንያት ተግባራዊነቱ እንዲቆም ወይም እንዲቋረጥ ሲደረግ የስምምነቱን ዋነኛ ጥሰት ስለሚያሳይ ሌላው ወገን ሊሽረው (Null and void) ይችላል ማለት ነው።

የሁሉም ስምምነቶች መሰረት የሆነው የ 1900 ውል አንቀፅ 2፤ "የጣሊያን መንግስት ቀጥሎ በተዘረዘሩት አካባቢዎች ለየትኛውም ሌላ ኃይል ላለመሸጥ፣ ላለመስጠት ራሱን ያስገዛል" ይላል። በዚህ መሰረትም ጣልያን በሁለተኛ ዓለም ጦርነት ሲሸነፍ ግዛቶቹ ለኢትዮጵያ ማስረከብ ነበረበት። በአፄ ሃይለስላሴ የሚመራው የኢትዮጵያ መንግሰት ኤርትራ በፌዴሬሽን ኢትዮጵያን ሰትቀላቀል (የኤርትራና ኢትዮጵያ ፌዴሬሽን አይደለም) ግዜ ጣሊያን ያፈረሰቻቸውን ስምምነቶች እንደማይሰሩ አውጀው ውድቅ አድርገዋል።

በወቅቱ ተረቀ በታወጀው የኤርትራ ህገመንግስት መሰረት የ 1900፣ 1902 ዎቹ እና 1908 የኢትዮጵያና ጣሊያን ስምምነቶች ውድቅና የማይሰሩ እንዲሆኑ አድርገዋል። እነዚህ የ 1900 ውሎች በ 1947 ቱ የፓሪሱ የሰላም ጉባኤ እና የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሀሳብ መሰረት የማይሰሩ ሆነዋል። ውልን ኣንድኛው ወገን ሲጥሰው ሌላኛው ተዋዋይ ያለው ውድቅ የማድረግ መብት በሚመለከት የሙኒክ ስምምነት እና የሪጋ ውል በሚል የሚታወቁት ዓለማቀፍ ውሎች ህያው ምስክሮች ናቸው። የሙኒክ ስምምነት የታላቅዋ ብሪታንያ፣ ጀርመን፣ ፈረንሳይ እና ጣሊያን ከቀድሞዋ ቼኮስላቫኪያ የሱድተን ላንድ ግዛቷን ወደ ጀርመን መቀላቀል በተመለከተ መስከረም 29/1938 በጀርመኗ ሙኒክ ከተማ ያደረጉት ስምምነት ነው።

ስምምነቱ ቼኮዝላቫኪያን ከጀርመን ወረራ ለመታደግ ለተፈጠረው አዲስ ወሰኖች አለማቀፍ እውቅና (ማረጋገጫ) በመስጠት የሁለተኛው የአለም ጦርነትን ለማስቀረት የተደረገ ነበር። ይሁን እንጂ ጀርመን ቼኮዝላቫኪያን በመውረር ሀገሪቱን በሙሉ ያዘች። ጀርመን ሆን ብላ ስምምነቶችን በመጣሷ የፈረንሳይ የታላቅዋ ብሪታንያ መንግስታት የሙኒክ ስምምነት የማይሰራ እና ውድቅ መሆናቸውን አውጇል። ከዚያ ስምምነት ጋር የተያያዘ የትኛውም ተግባር የሚያስከትለው ውጤት (ለውጥ) በሙሉ ውድቅ ማድረጋቸውን ገልፀዋል። በመሆኑም የሀገሪቱ ድንበር ከመስከረም 1938 በፊት በነበረው የቼኮዝላቫኪያ ሪፐብሊክ ወሰን እንደሚሆን አረጋግጠዋል።

የ 1921 ሪጋ ስምምነት ሶቪየት ህብረት ከጥቅምት አብዮት እና ከፖላንድ ጦርነት በኋላ ተዳክማ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነበረች። ወታደራዊ ኃይሏንም ከድንበር አካባቢ የመለሰች በመሆኑ በአወዛጋቢ የድንበር አካባቢዎች የግዛት ማካካሻ ለመስጠት ከፖላንድ ጋር በ 1921 የሪጋ ስምምነት ተፈራርመች። በመስከረም 28/1939 ሶቪየት ህብረት የሪጋ ስምምነትን በተናጥል በመጣስ ከጀርመን ጋር ፖላንድን ለመቀራመት ተስማሙ። በሰኔ 22/1941 የጀርመን ወታደራዊ ኃይል ሶቪዬት ህብረትን ወረረ። በሰኔ 30/1941 ደግሞ ሶቪዬት እና ፖላንድ ጀርመንን ለመውጋት ሲስማሙ። የ 1921 ሪጋ ስምምነትንም ታደሰ። ሆኖም ከጥር 11,1944 በኋላ ሶቪየት ህብረት ከአሜሪካ እና ከእንግሊዝ ጋር ገብታው በነበረው ውል እንደገና ታድሶ የነበረው የሪጋ ስምምነት በፖላንድ ጭምር

ውድቅ እንዲሆን ተደርጎ ተጠናቋል።

ሶቪዬቶች ይጠይቁት የነበረው የኩርዘን መስመር የፖላንድና ሶቪዬት ድንበር እንዲሆን እንግሊዞች ባቀረቡት ምክረ-ሀሳብ የሪጋ ስምምነትን ሻሩት። ኢትዮጵያ በ 1928 በጣሊያን ወረራ ሲፈፀምባትና ስትያዝ የ 1900 ዎቹ ስምምነቶች ውድቅ የማድረግ መብት በሚገባ የሚገልፁ ሲሆን የሁለተኛው የአለም ጦርነት ለማስቀረት እንዲሁም ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን የወሰን መብቶችን ለድርድር ስለማቅረብ እንዲሁም ከጦርነቱ በኋላ በወሰን አከላለል ስራዎች ውስጥ ወታደራዊ ኃይል ያለውን ሚና እና ለፖሊሲ አላማዎች እንደ ሁኔታዎች የታየው መለሳለስ ከላይ ካነሳናቸው ተግባራት ትምህርት የሚወሰድባቸው ናቸው።

## የ 1900 ዎቹ ውሎች ውድቅ ከሆኑ ኤሪትራ ነፃ ስትወጣ ድንበሩ በየትኛው ዓለማዊ ህግ ይገዛል?

በየካቲት 10/1947 ከጣሊያን ጋር የተደረሰው የሰላም ውል ስምምነት ጣሊያን በአፍሪካ ያሏትን ግዛቶች ማለትም ሊቢያ፣ ኤርትራ እና የጣሊያን ሱማሌላንድ ሙሉ መብትና ባለቤትነት እንድትለቅ የሚያደርገው ይገኝበታል። ኢትዮጲያ ከአምስት ዓመት ትግል ነፃነትዋን በማረጋገጥዋ ጣሊያን በግዛቶቿ ላይ የነበሯትን መብቶች እና ኃላፊነቶች በሰላም ስምምነቱ አንቀፅ 23 መሰረት ሰጥተው በኢትዮጵያና ጣሊያን መካከል የነበረው ውል ማብቂያ ሆነዋል።

በኢትዮጵያ እና ኤርትራ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከተው ሌላ አዲስ ሕጋዊ ማዕቀፍ (Legal Regime) ተመሰረተ። አቃፊው ሕግ "በተባበሩት መንግስታት እና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገ ስምምነት" ሆነ። በግልፅ ለማስቀመጠም በ 1952 ኤርትራን በፌደሬሽን ከኢትዮጵያ ያዋሃደው" የሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊ ኃያላን መንግሰታት እና የኢትዮጵያ ስምምነት" ነው። የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ምክረ ሃሳቦች ከራሱ ከመንግስታቱ ድርጅት ውጭ አስገዳጅ ህጋዊ ውጤት ያላቸው አይደሉም። ይሁን እንጂ ጣሊያን በቅኝ ግዛቶቿ ላይ ያላትን መብት የወረሱት አሸናፊዎቹ ኃያላን መንግስታት ለጠቅላላ ጉባኤ ስለወከሉት (delegate)ና ሃሳቡን በመቀበል ስለተገበሩት ነው። በመሆኑም በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ - ኤርትራ 390A መሰረት ኤርትራ ራስ ገዝ ሆና በኢትዮጵያ ዘውድ ስር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀል የተደረገበትን የፌደሬሽኑን መሰረታዊ መርሆዎችና እምነቶች ናቸው አቃፊው ሕግ የሚሆኑት።

የውሳኔ የፍላጎት መንፈስ (intent) ለመረዳት የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ በመስከረም 24/1948 ባካሄደው 143 ኛው ስብሰባ፣ የቀረቡ አስተያየቶች በዋናነት ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ማቀላቀል ላይ ያተኮሩት ማየት ተገቢ ነው። ነገር ግን በትክክል የትኞቹ ግዛቶች እንደሚካተቱ ሡፌ አለመግባባት ነበር።"

ሀ/ የኤርትራ ምስራቃዊ ክፍል ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል አለበት፣ ቀሪው የምዕራቡ ክፍል ሌላ መፍትሄ ይፈለግለታል። (ታላቅዋ ቢሪታንያ እና አሜሪካ)

ለ/ ሁሉም የኤርትራ ክፍል በፍጥነት ወደ ኢትዮጵያ መተላለፍ አለበት። (ላይቤሪያ እና ኢትዮጵያ)

ሐ/ በባለ አደራ ምክር ቤት በሚሾም አስተዳደር በተባበሩት መንግስታት ባለአደራነት ስር ሆኖ በአማካሪ ኮሚቴ ድጋፍ ይደረግ። ኢትዮጵያ በአሰብ በኩል የባህር በር እንድታገኝ የግዛት ማካካሻ ይደረግላት። (ሶቪየት ህብረት፣ ዩጎዝላቪያ፣ ቼኮዝላቫኪያ፣ ፖላንድ፣ ቤይሎሩስያን፣ ዩክሬን)

መ/ የስሜን ኤርትራ ክፍል በጋራ (በህብረት) ባለ አደራ አስተዳደር ስር ሆኖ ጣሊያን ባላአደራ አስተዳደር ትሁን። የደቡብ የሀገሪቱ ክፍል ወደ ኢትዮጵያ ይጠቃለል (አርጀንቲና ቱርክ)።

ሠ/ የባህር በር የማግኘት ጉዳይ እንዳለ ሆኖ ዘርን እና ኃይማኖትን መሰረት በማድረግ የተወሰነው የኤርትራ ክፍል ወደ ኢትዮጵያ መጠቃለል አለበት። ቀሪው የሀገሪቱ ክፍል ጣሊያን አስተዳዳሪ ሆና በተባበሩት መንግስታት ባለ አደራነት ስር መሆን አለበት። (ቤልጂየም፣ ቺሊ፣ ኮሎምቢያ፣ ኮስታሪካ፣ ዶሚኒካን ሪፐብሊክ፣ ኢኳዶር፣ ኤልሳቫዶር፣ ጓቲማላ፣ ሆንዱራስ፣ ፓናማ፣ ፓራጓይ፣ ፔሩ፣ የደቡብ አፍሪካ ህብረት፣ ቬንዙዌላ)።

የጣሊያን ግዛቶችን በተመለከተ ኃላፊነት የወሰዱት ኃያላን መንግስታት በተጠቀሱት ግዛቶች መለቀቅ ዙሪያ ድርድር የማድረግ እና መፍትሄ የማምጣት ኃላፊነት ነበር የወሰዱት ። ነገር ግን በማስለቀቁ ጉዳይ ላይ መስማማት አልቻሉም።

ታላቅዋ ብሪታንያ

(1) ኢትዮጵያ ለአስር አመታት ያህል ኤርትራን ለማስተዳደር መመደብ አለባት።

(2) ከአስር አመት በኋላ የኢትዮጵያ አስተዳደር በምን ሁኔታ ለዘለቄታው መቀጠል እንደሚችል የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ ይወስናል።

(3) የኢትዮጵያን አስተዳደር የሚደግፍ የአማካሪዎች ምክር ቤት ይመደባል። ምክር ቤቱ ኤርትራዊያንን፤ የአራቱ ኃያላን ወኪሎችን እንደዚሁም ከጣሊያን፣ ሲውዘርላንድ፣ አንድ የስካንድኔቪያን አገር እና አንድ የሙስሊም አገርን ያካተተ ይሆናል።

ፈረንሳይ

(1) ከዙላ ባህረሰላጤ እስከ ፈረንሳይ ሱማሌላንድ ካለው ግዛት ውጭ ያለው የኤርትራ ክልል በጣሊያን ሞግዚትነት መያዝ አለበት።
(2) ከዙላ ባህረ ሰላጤ እስከ ፈረንሳይ ሱማሌላንድ ያሉት ግዛቶች ከሙሉ ሉአላዊነት ጋር ለኢትዮጵያ መሰጠት አለበት። (3) ለኢትዮጵያ በተሰጡት ግዛቶች እና በጣሊያን ሞግዚትነት ስር ባሉት ግዛቶች መካከል ያለው ድንበር የአካለ ጉዛይ ምስራቃዊ አስተዳደራዊ ወሰንን ተከትሎ ከዙላ ባህረ ሰላጤ እስከ አሁኑ የኢትዮጵያ ድንበር ያለውን የያዘ መሆን አለበት። ከኢትዮጵያና ጣሊያን ወገን በዕኩል በሚወከሉ ሰዎች አማካኝነት ወሰን የማካለል ስራው ከመስከረም 15/1949 በፊት መጠናቀቀ አለበት። አሜሪካ የደቡባዊ ኤርትራ ክፍል ወደ ኢትዮጵያ እንዲጠቃለል ሀሳብ ታቀርባለች። ይህ አካባቢ የደናከል ዳርቻ የአካለ ጉዛይ እና ሰራይ ግዛቶችን በማካተት አዲሱ ድንበር ከዙላ ባህረ ሰላጤ የአካለ ጉዛይ እና ሰራይ ሰሜናዊ ድንበርን ተከትሎ እስከ ኢትዮጵያ ድንበር ያለውን ይይዛል።

ጣሊያንም ብትሆን ይሄንን መብት እውቅና መስጠት ነበረባት። የመጀመሪያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ጉባዔ በለንደን ከመደረጉ አስቀድሞ የጣሊያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለአሜሪካ አቻቸው ተከታዩን መልዕክት ፅፈው ነበር። "በሶማሊላንድ ሞግዚትነት (የባለአደራ ስርዓት) ላይ የሚመከር እንኳ ቢሆን የረጅም ጊዜ ቅኝ ግዛታችን በሆነችው ኤርትራ የጣሊያን ሉአላዊነት መጠበቅ ተገቢ ነው። ይህ የኢትዮጵያን የባህር በር የማግኘት ጥያቄ የሚያካክስ ነው። ለዚያ ብለንም ከደሴ ወደ አሰብ የሚወስድ መንገድ ገንብተናል። ይህ መብት ሊረጋገጥ የሚችለው በጣሊያን ግዛት ውስጥ አሊያም ጥያቄው ከቀረበ ደግሞ በድንበር ማካለል (rectifications) ነው።

በኢትዮ-ኤርትራ ጉዳይ የተባበሩት መንግስታት ውሳኔ 390 v መግቢያ እንደሚከተለው ይላል። ከዚህ የሚከተለውን ከግምት በማስገባት፤

ሀ/ በኤርትራ የተለያዩ ብሄረሰቦች፣ የሀይማኖትና ፖለቲካ ቡድኖች አስተያየት እና የህዝቡ ራስን የማስተዳደር አቅምን ጨምሮ የኤርትራ ነዋሪዎች ፍላጎትና ደህንነት

ለ / የምስራቅ አፍሪካ ሠላምና ፀጥታ ሁኔታዎች

ሐ/ ከመልክአምድር፣ ከታሪክ፣ ከብሄረሰቦች እና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች በመነሳት በተለይም የኢትዮጵያን ህጋዊ የባህርበር የማግኘት ጥያቄ እና መብቶች።

መ/ የውጭ ሀይሎች ለኤርትራ ኢኮኖሚ ልማት የሚኖራቸውን ቀጣይነት ያለው ትብብር የማረጋገጥ ጠቀሜታን ከግምት በማስገባት
ሠ/ የኤርትራ መለቀቅ ከኢትዮጵያ ጋር ቅርበት ያለው ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚ ውህደትን መሰረት ማድረግ እንዳለበት እውቅና በመስጠት
ረ/ የዚህ የውህደት ስምምነት ፍላጎት ለኤርትራ ነዋሪዎች፣ ተቋማት፣ ሀይማኖት፣ ቋንቋዎች እና ልማዶች ሙሉ ክብር እና ጥበቃን ለማረጋገጥ ብሎም ሰፋት ያለው ራስን የማስተዳደርና በተመሳሳይ የኢትዮጵያን ህገመንግስት፣ ተቋማት፣ ልማድ እና አለማቀፍ እውቅና እና ተቀባይነት በማክበር ነው ይላል። የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ በኤርትራ ኮሚሽን ሪፖርት ላይ የጠቅላላ ጉባዔው ጊዜያዊ ኮሚቴ ሪፖርት መሰረት 390-A(V) የውሳኔ ሀሳብን አሳለፈ። በዚህ ውሳኔም ኤርትራ ራስገዝ ሆና ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀልና በኢትዮጵያ ዘውድ ሉአላዊነት ስር እንድትሆን ውሳኔ አሳለፈ።

የውሳኔ ሀሳቡ (390v) በአጠቃላይ አለማቀፍ ህግን ተከትሎ እና በተለይ ደግሞ የቬይና የውሎች ህግ ድንጋጌን መሰረት ተደርጎ ሊተረጎም ይገባዋል። የቬይና ድንጋጌ የውሎች ህግ አንቀፅ 31(1) እንደሚያትተው "አንድ ውል በመልካም ጎኑ መተርጎም ይኖርበታል። የውሉ ቃላቶች በመደበኛ የአውድ ይዘታቸው እንዲሁም ጭብጥ እና ፍሬ ነገር መሰረት በማድረግ ሊታይ ይገባል። "በአንቀፅ 31(1) የሰፈሩት መሰረታዊ መርሆዎች የቀናነት መርህ፣ መደበኛ ትርጉም፣ አውድ፣ ጭብጥ እና ፍሬ ነገር ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች በቬይና ድንጋጌ የውሎች ህግ አንቀፅ 31 መሰረት የኤርትራን ሁኔታ በተመለከተ በአራቱ ኃያላን እና ኢትዮጵያ መካከል የተደረሰው ውል ዋና ዓላማ እና ተግባር የኢትዮጵያን ሰላም ለማስጠበቅ እና የባህር በር ባለቤትነት መብቷን ያረጋግጣሉ። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እስከተቀላቀለችበት ጊዜ ድረስም በወቅቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኋላም ጠቅላይ ሚኒስቴር በነበሩት አክሊሉ ሀብተወልድ የሚመራ የኢትዮጵያ ልዑክ ኤርትራ ለማስመለስ ካልተቻለም የሀገሪቱን የባህር በር መብት ለማረጋገጥ ታግሏል። የአዲሱ ስምምነት ተዋዋዮች ማለት ኢትዮጵና የአሸነፊዎቹ ኃያላን መንግሰታት ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ በፌዴሬሽን ሲቀላቅሉ አንዱ ታሳቢ የተደረገው የኢትዮጲያ ሉዑላዊ የባህር በር የማግኘት መብት ነው። ከእንግዲህ ወዲህ ከኤርትራ ጋር የሚድረግ ማናቸውም ድንበር ማእከል የሚያደረግ ድርድር የኢትዮጲያ ሉዑላዊ የባህር በር የማግኘት መብት ማእከል ያደረገና በድንብር አከባቢ የሚኖሩት የሁለቱ አገር ህዝቦች ፍትሓዊ ውሳኔ የሚገኙበት ሊያሠራ የሚያስችል ዓለማዊ ሕግ (applicable international law) መስረት መሆን ይገበዋል።

## የአልጀርስ ስምምነት ለመሰረዝ ሕጋዊ መበት አለን

ይህ ስምምነት ወራሪ እና ተወራሪ አሸናፊ እና ተሸናፊ እኩል የሚያደርግ መሆኑ አሳፈሪ ቢሆንም የአገራችንን መብት አሳልፎ የሰጠ በመሆኑ ዘላቂ ሰላም ሊያረጋግጥ አይችልም:: በኢትዮጵያ አጠቃላይ ደህንነት በተለይም በኢኮኖሚ ደህንነት አደጋ ውስጥ የሚያስገባ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ እና ክብር የማይመጥን ስምምነት ነው። የኤርትራ መንግስት ጦርነትን ጫረ፤ ተሸነፈም። ኤርትራ ያደረሰው ጥፋት ጦርነቱን በመጀመሩ ተጠያቂ መሆን ነበረበት፣ ወራሪ በመሆኑም ሰራዊቱ ለመወረር በማያስችለው መገደብ ነበረበት ከዛ በላይ ለስምምነቱ መነሻ ሃሳብ ሲቀርብ ማእከሉ የሉዑላዊ ባህር በር ጉዳይ መሆን ነበረበት።ካልተቀበለ ቅጣቱ ከፍተኛ ይሆን ስለነበር የኤርትራ መንግሥት ከመቀበል ውጭ ሌላ አማረጭ አልነበረውም።

## የአልጀርስ ስምምነት ሕጋዊ ውል ነው ወይ?

በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 225/1993 "የኢትዮጲያ ፌዴራለዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ና በኤርትራ መንግስት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ" የሚል ሲሆን የታወጀበት ወቅት ሕዳር 29 ቀን 1993 (8/Dec/2000) ነው። የአልጀርስ ስምምነት የተፈረመው ግን ታሕሳስ 3 ቀን 1993 (12/Dec/2000) ከአራት ቀን በኋላ ነው። እንደሚታወቀው በአልጀርስ ስምምነቱ እስኪቋጭ ድረስ ድርደር ነበረበት። በሕገ-መንግስታችን አንቀጽ 55 (12) "የሕግ አስፈጻሚው አካል የሚዋዋላቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ያጸድቃል ይላል" ሕገ መንግስታችንን ይፃረራል። ከሕገ-ፍልስፍናም (Jurisprudence) አኳያም ሕግ- አወጭው ስልጣኑን አሳልፎ መስጠት የተከፋፈለ መንግስትን መርህ ይፃረራል። ተዋዋዮች ሁሉ ስምምነቶቹ በየሃገሩ ባሉት ስርዓቶች መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። በዚህም ምክንያት ሕጋዊነቱ ላይ ጥያቄ ያስነሳል።

ውሉ ሕጋዊ ቢሆን እንካን ገና ከመጀመሪያው የኤርትራ መንግስት ማፍረስ በመጀመሩ ኢትዮጲያ ለመሰረዝ (Null and Void) ለማድረግ ሕጋዊ መሰረት አላት። የአልጀርስ ስምምነት አንፃር በአንቀጽ I (1 እና 2) ናቸው። ዋና ዓለማው በሁለቱ አገሮች ስላም ማስፈን ነው። የድንበር፣ የካሣ ወ.ዘ.ተ ጉዳዮች የመጨረሻ ግባቸው ስላም ማረጋገጥ ነው።

Article I

1. The parties shall permanently terminate military hostilities between themselves. Each party shall refrain from the threat or use of force against the other.

2. The parties shall respect and fully implement the provisions of the Agreement on Cessation of hostilities.

በንኡስ አንቀጽ ሁለት የተጠቀሰው ተፃብኦን ለማቋረጥ (Cessation of hostilities) የ 25 ኪሎሜትር ጊዜያዊ የደህንነት ቀጠና

(Temporary Security Zone) የጦርነት ኣደጋ ለመቀነስ (buffer zone) ተመስርቶ ይህንን የሚጠብቅ የ ተባበሩት የሰላም እስከባሪ ይጠበቀዋል ይላል። የኤርትራ መንግሥት ከተወሰኑት ወራት በኋላ የሰላም እስከባሪ ሓይሉን በማበረር ጊዜያዊ የደህንነት ቀጠናውን አፈርሶ ወታደሮችን አሰፈረ።

ንኡስ አንቀጽ አንድን በመፃረር የኤርትራ መንግሥት ኢትዮጵያን ለማተራመስ በማስብ እና በመንቀሳቀስ ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ስጋት ሆነዋል። በኤርትራ ውስጥ ፀረ- ኢትዮጲያ ኃይሎችን በማሰበሰብ፤ በማሰልጠን፤ በማስታጠቅ እና በማሰማራት ቀጣይነት የለው ትንኮሳ እየፈፀመ ይገኘል። በሶማልያ በኩል-----(proxy war) በተደጋጋሚ በመክፈት ኢትዮጵያን የማተራመስ ዕቀዱን እስከ ቅርብ ጊዜ ያካሂደው ነበር። የቀድሞ ጠ/ሚኒስተሮች በየጊዜው በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሲየሰሙት የነበረት ስሞታዎች እና የተባበሩት መንግስታት ሪፖርቶች እና እነሱን መሰረት አድርጎ የጣለው ማዕቀቦች በቂ ማስረጃዎች ናቸው። አንድ ምሳሌ ብንወስድ፤ በፀጥታው ምክር ቤት የውሳኔ ሀሳብ 1676 (2006) መሰረት የቀረበው የተባበሩት መንግስታት የሶማሊያ ተቆጣጣሪ ቡድን ሪፖርት እንደሚከተለው ይላል።

" ጅቡቲ፣ ግብፅ፣ ኤርትራ፣ ሊቢያ፣ እና የተወሰኑ የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች የተባበሩት እስላማዊ ፍርድ ቤትን በተለያዩ የፀረ ታንክ፣ ፀረ አውሮፕላን፣ እና ሌሎችም መሳሪያዎች በማስታጠቅ እንዲሁም በሎጅስቲክስ (ቁሳቁስ) ድጋፍ እና ማማከር እያገዙ ናቸው። የቡድኑን ድጋፍ በማስተባበር እና ማስተላለፍ ዋነኛ ድልድይ ሆኖ እያገለገለች ያለችውም ኤርትራ ነች።

እላይ በዝርዝር እንደተገለፀው አንዱ ተዋዋይ ወገን ውሉን ካፈረስ ሌላኛው ወገን የመሰረዝ መብት በመኖሩ ኢትዮጵያ ስምምነቱን የማፍረስ ሕጋዊ መብት ስላላት ሰሪዣለሁ ብላ ማወጅ አለባት።

መጠቃለያ

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ የምስራቅ አፍሪካ የፖለቲካና ኢኮኖሚክ ሕብረት አስተሳሰብዎ የሚደነቅ ነው። ይህ ግን በረዥም ጊዜ የሚፈጸም ስራ ነው። ከአሁኑ መጀመር ቢኖርበትም ብዙ ውጣ ውረድ አለበት የአካባቢያችንን ሀብትና ወታደራዊ አቅማችንን እያፈረጠሙ ያሉት ሀገራት ብዙ መሰናክል ይፈጥራሉ። አብዛኛው በአካባቢያችን ያሉ አገሮች በነሱ ተጽዕኖ ስር የወደቁ ናቸው። በራሳቸው የሚወስኑ አይደሉም።ኢትዮጵያ የባህር በር ጉዳይ ከኤርትራ ብቻ ሳይሆን ከጂኦ ፖለቲክስ መታየት አለበት።

የአልጀርስ ስምምነት ኢትዮጵያን ከድል መንጋጋ ሽንፈት እንድትወስድ አድርጓል። ያረጁ የወደቁ እና የተተኩ የ 1900 ዎቹ ውሎች በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የድንበር ጉዳየ መደራደሪያ ሊሆኑ አይችሉም። አቃፊው ሕግ "በተባበሩት መንግስታት እና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገ ስምምነት" ሆነ። በግልፅ ለማስቀመጠም በ 1952 ኤርትራን በፌደሬሽን ከኢትዮጵያ ያዋሃደው " የሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊ ኃያላን መንግሰታት እና የኢትዮጵያ ስምምነት" ነው። የአልጀርስ ስምምነት ሕጋዊ ውል አይደለም።

ኤርትራም በተዳጋጋሚ የጣሰችው በመሆኑ ኢትዮጲያ የመሰረዝ መብት አላት። በርካታ ምሁራን ኢትዮጵያ ሉዑላዊ የባህር በር መብት በሚመለከት በጥናታቸው አረጋግጠዋል። ለጊዜውም ቢሆን ሉዓላዊ የባህር በር የማግኘት መብቷን እና ሌሎች የውስጥ ግዛቶቿን አጥታለች ከእንግዲህ ወዲህ ከኤርትራ ጋር የሚደረግ ማናቸውም ድንበር የማካለል ድርድር የኢትዮጵያ ሉዑላዊ የባህር በር የማግኝት መብት ማዕከል ያደረገና በድንብር አካባቢ የሚኖሩት የሁለቱ አገር ህዝቦች ፍትሓዊ ውሳኔ የሚገኝበት ሊያሠራ የሚያስችል በዓለም ዓቀፍ ሕግ (applicable international law) መሰረት መሆን ይገባዋል። ለጊዚያዊ ፖለቲካ የአገራችንን ዘላቂ መብትና ጥቅም አናጥፋው። የአልጀርስ ስምምነት ለማሽቀንጠር ግዜው አሁን ነውና!!